ለጥቃት ጥበቃ ያሻል: ሞጁል 1

ከጥቃት ጥበቃ፡- መጀመሪያ

በጥቃት ጥበቃ ዙሪያ ከተዘጋጀው ባለአምስት ክፍል የበይነ-መረብ ተከታታይ ትምህርት ውስጥ ይህ የመጀመሪያው ሞጁል ነው። ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተገናኙ ተጨባጭ ጉዳዮች ላይ የሚሠራ ፋሚሊ ሄልዝ ፍሮንቲየርስ (ኤፍ. ኤች. ኤፍ) የተባለ ምናባዊ ብሔራዊ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅትን ታሪክ መሠረት በማድረግ ተከታታይ ትምህርቱ ከጥቃት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ቁልፍ ፅንሰ-ሃሳቦችን ያስተዋውቃል።

መግቢያ

አጠቃላይ ሁኔታ/የመነሻ ዓውድ

የሥራ ቦታ ባህሪያት

ማጠቃለያ

መግቢያ

ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ይህ ሞጁል የሚከተሉትን ለማድረግ ይረዳዎታል፡-

- ከጥቃት ጥበቃ/ከለላ ጋር የተያያዙ ቃላትን ለመተርጎም፡፡
- በአንድ ድርጅት ውስጥ ከጥቃት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ኃላፊነቶችን ለመረዳት፡፡
- የሥራ ቦታ ባህሪያት ለጥቃት ጥበቃ ያላቸውን አስፈላጊነት መገንዘብ፡፡

የጥናት ጊዜ፡- 30 ደቂቃዎች

ሞጁሉ ሁለት ክፍሎች አሉት፡-

ክፍል 1- የመነሻ ሁኔታ/ዐውድ

ስለፋሚሊ ሄልዝ ፍሮንቲየርስ (ኤፍ.ኤች.ኤፍ) እና ስለቡድኑ ትውውቅ፡፡ ከጥቃት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ጠቃሚ ፅንሰ ሀሳቦችንና ትርጓሜዎችን እንድትተዋወቁ ይረዷችኋል፡፡

ክፍል 2 - የሥራ ቦታ ባህሪያት

የኤፍ.ኤች.ኤፍ ቡድን የሥራ ድርሻዎችን፣ ከጥቃት ጥበቃ ጋር የተገናኘ ኃላፊነታቸውን እና የሥራ ቦታ ባህሪያትን መፈተሽ፡፡

አጠቃላይ ሁኔታ/የመነሻ ዓውድ

ፋሚሊ ሄልዝ ፍሮንቲየርስ

ፋሚሊ ሄልዝ ፍሮንቲየርስ (ኤፍ.ኤች.ኤፍ) ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተገናኘ በሚያደርገዉ የመጀመሪያ ምዕራፍ ዘመቻ ላይ አብረው እንዲሳተፉ ጋብዘዎታል። በሞጁሉ የመጀመሪያ ክፍል፣ የኤፍ.ኤች.ኤፍ ቡድን ከጥቃት ጥበቃ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጠቃሚ ፅንሰ-ሃሳቦችና ትርጓሜዎች ያስተዋውቅዎታል። ስለ ኤፍ.ኤች.ኤፍ ውስጣዊ የተቋም እንቅስቃሴና ውጫዊ ስጋቶች መረጃ ይኖርዎታል። የሥራ ቦታ ባህርያትን ለመፈተሽ እና እነዚህንም ባህርያት ከጥቃት ጥበቃ በምን መንገድ መልክ ሊያሲዛቸው እንደሚችል ለመረዳት ተጨማሪ ዕድል ሊፈጥርልዎት ይችላል።

ፋሚሊ ሄልዝ ፍሮንቲየርስ (ኤፍ.ኤች.ኤፍ) የጤና እንክብካቤ አገልግሎት በመስጠት ዕውቅና ያለው መካከለኛ ደረጃ የሲቪል ማኅበረሰብ ተቋም ነው።

ኤፍ.ኤች.ኤፍ የሚገኘዉ/የሚንቀሳቀሰው ጉልህ የሆነ የደህንነት ስጋት ባለበት ሀገር ነው። ሀገሪቱ ድህነት የተንሰራፋባት እና በአብዛኛዉ የገጠሩ ክፍል ደካማ የትምህርት ተደራሽነትና የመጀመርያ የጤና አጠባበቅ አገልግሎት የሚገኝባት ናት። የሕግ ማዕቀፎች ግለሰቦችን ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለመከላከል የማያስችሉና ደካማ ናቸው። በሥራ ላይ ያሉት ሕጎችም በደንብ የማይተገበሩና በቀላሉ ሊጣሱ የሚችሉ ናቸው።

ኤፍ.ኤች.ኤፍ 25 የሀገር ውስጥ ሠራተኞች አሉት። በሞጁሎቹ ውስጥ እየሠራችሁ በቆያችሁ ቁጥር የተወሰኑ ሠራተኞችን በተለይ ደግሞ ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ ኃላፊነት ያለባቸውን በደንብ ልታውቋቸው ትችላላችሁ።





"ሰላም፣ እኔ ዝናሽ ሀፍቶም እባላለሁ። የኤፍ.ኤች.ኤፍ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኜ በቅርቡ ተሾሜያለሁ። ጥሩ የሆነ ሞያ-ነክ የግንኙነት መረብ አለኝ በመሆኑም ትክክለኛ ከሆኑ ሰዎች ጋር ትስስር እንዳለኝ ይሰማኛል። ታማኝነትና ጠንክሮ መሥራት አስፈላጊ እንደሆነ አምናለሁ። ለማሳበራዊ ፍትህ ጠንካራ ተከራካሪ ነኝ። የድርጅቱ ዋና ኃላፊ እንደመሆኔ መጠን ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተገናኘ የመጨረሻ የተጠያቂነት ኃላፊነት አለብኝ።"

"ሰላም፣ እኔ ዚነት ሙሀባ እባላለሁ። የሰው ሃብት ልማት ባለሞያ ነኝ፣ ኤፍ.ኤች.ኤፍ በማሳበረሰብ ጤና አጠባበቅ ላይ እየሠራ ስላለው ሥራ ፍቅር አለኝ። መሥራት ያለብኝ የሥራ መጠን አብዛኛውን ጊዜ እንድጨነቅ ያደርገኛል። ከጥቃት ጥበቃ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ አስባለሁ። ነገር ግን ገና ብዙ መማር የሚገባኝ ነገር አለ። ለኤፍ.ኤች.ኤፍ የጥቃት ጥበቃ ተጠሪ ልሆን እችላለሁ።"

"ሰላም፣ እኔ አህመድ መሐመድ እባላለሁ። ልምድ ያለኝ የፕሮጀክት ማናጀር እና የፕሮግራሞች ኃላፊ ነኝ። በጣም ስልታዊ ስሆን ትክክለኛ ከሆኑ ሰዎች ጋር እንዴት ግንኙነት መመሥረት እንዳለብኝ ጠንቅቄ አውቃለሁ። እንደ ኤፍ.ኤች.ኤፍ ያሉ ድርጅቶችን በቅርቡ እንደምመራ ተስፋ አለኝ። ደህንነቱ የተጠበቀ ፕሮግራም አስተዳደር እንዲኖር የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብኝ።"

"ሰላም፣ እኔ አስቴር ዘማችእባለለሁ። የፕሮግራም ኦፊሠር ነኝ። በሥራዬ ኩራት ይሰማኛል፣ ሥራዬንም በአግባቡ እንደምሠራ ሰዎች ይነግሩኛል። ሞያዬን የማሳደግ ፍላጎት አለኝ ስለሆነም አዳዲስ ፈተናዎች ያስደስቱኛል። በፕሮግራም ማዕቀፌ ውስጥ የጥቃት ጥበቃ እርምጃዎችን ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት አለብኝ።"

"ጤና ይስጥልኝ እኔ አሰፋ ጌታቸው እባላለሁ። በኤፍ.ኤች.ኤፍ ውስጥ የክትትል፣ ምዘና እና ትምህርት ባለሞያና መሪ ነኝ። ለረዥም ዓመታት ለኤፍ.ኤች.ኤፍ በመሥራት ላይ እገኛለሁ፣ በሥራዬም ደስተኛ ነኝ። ጠንካራ የሥራ ግንኙነቶች ለእኔ ወሳኝ ናቸው። ጀማሪ ሠራተኞች እኔን ይመለከታሉ። በክትትል፣ ምዘና እና ትምህርት ትግበራዎች ላይ የጥቃት ጥበቃ ጉዳይ መካተቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብኝ።"

"ሰላም፣ እኔ ደስታ ውሂብ እባላለሁ። የክትትል፣ ግምገማ ምዘና እና ትምህርት ኦፊሠር ነኝ። ለሥራዬ ከፍተኛ ግምት እና ፍቅር/ጥልቅ ስሜት አለኝ። በድጋፍ ሰጭ ቡድን ውስጥ መሆኔን እወደዋለሁ። ብዙ ባይሆንም የተወሰነ የቀደመ የሥራ ልምድ አለኝ። ብዙ መማር ያለብኝ ነገር እንዳለ አውቃለሁ። በክትትል፣ ምዘና እና ትምህርት ትግበራዎች ውስጥ የጥቃት ጥበቃ ጉዳይ እንዲካተትና ተያያዥነት ያላቸው ስጋቶች እንዲቀንሱ ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለብኝ።".”

ሙሉዉን መመልከት ይችላሉ የመረጃና ከጥቃት ጥበቃ ማዕከል የጥቃት ጥበቃ የሥራ እንቅስቃሴ

የጥቃት ጥበቃ ትርጓሜዎችን ማስተዋወቅ

ከጥቃት ጥበቃ ማለት ምን እንደሆነ በትክክል መረዳት በኤፍ.ኤች.ኤፍ የጥቃት ጥበቃ እንቅስቃሴ ውስጥ አስፈላጊ የሆነ የመጀመሪያ ደረጃ እርምጃ ነው። ቁልፍ የሆኑ ትርጓሜዎችን መረዳት አስፈላጊ ነው።

ከጥቃት ጥበቃ ስንል ምን ማለታችን ነው?

ለኤፍ.ኤች.ኤፍ፣ ከጥቃት ጥበቃ የተዋቀረው ተያያዥነት ካላቸው ሦስት ጭብጦች ነው፦

- ከጥቃት ጥበቃ ማለት ወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃትና ወሲባዊ ትንኮሳ እና ሌሎች የጉዳት ዓይነቶች እንዳይከሰቱ ለመከላከል፤ ሰዎችን በተለይም ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ አዋቂዎችንና ህፃናትን ከእነዚህ ጉዳቶች ለመጠበቅ፤ እንዲሁም ጉዳት ሲከሰት በአግባቡ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ምክንያታዊና ተገቢ የሆኑ እርምጃዎች በሙሉ መውሰድ ማለት ነው። በሥራ ባልደረባ (ወይም ባልንጀራ) ወይም በተቋሙ የአሠራር ሂደቶች ወይም ፕሮግራሞች ሊደርስ ለሚችል ጉዳት መፍትሄ ይሰጣል።
- የወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን መከላከልና ሲፈፀሙ ምላሽ መስጠት የተቋማት ተቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል።
- በዚህ ሞጁል ውስጥ የተመለከቱት ሌሎች የጉዳት ዓይነቶች ኃይል መጠቀምና ማስገደድ፣ ትንኮሳ እና መድልዎ ሲሆኑ እነዚህም ከሥራ ቦታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ናቸው። በሠራተኞች ላይ የሚፈፀም ወሲባዊ ትንኮሳ በሥራ ቦታ ላይ የሚስተዋል ችግር ነው።

የጉዳትና ጥቃት ትርጓሜዎች

ወሲባዊ ብዝበዛ
ጥቃት ፈጻሚዉ ሥልጣኑን ወይም የተጣለበትን እምነት ያለአግባብ በመጠቀም ለወሲባዊ ዓላማ እና ለግላዊ ጥቅም ሲል የሚፈጽመው የወሲባዊ ብዝበዛ ዓይነት ነው። አብዛኛውን ጊዜ ወሲባዊ ብዝበዛ የሕግ ከለላ አለው።

ወሲባዊ ትንኮሳ
ግለሰቢ/ቡ ሃፍረት እንዲሰማት/ው ወይም እንድትሸማቀቅ/እንዲሸማቀቅ የሚያደርጉ የተለያዩ ተቀባይነት የሌላቸውእና ሰላስፈላጊ የሆኑ ወሲባዊባህርያት። አብዛኛውን ጊዜ ወሲባዊትንኮሳ የሕግ ከለላ አለው።

ትንኮሳ
የአንድን ግለሰብ ማንነት፣ ወይም እንዷ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ዘር፣ ብሄር፣ አካል ጉዳት፣ ሃይማኖት፣ የወሲብ ማንነት የመሣሥሉትን መለያዎችን መሠረት በማድረግ የሚረግ ኃይል አዘል ጥቃት ነው። አብዛኛውን ጊዜ ትንኮሳ የሕግ ሽፋን/ከለላ አለው።

ወሲባዊ ጥቃት
ኃይል በመጠቀም፣ በዛቻና በማስፈራራት ወይም ፈቃዱን መስጠት በማይችል ተጎጂ ላይ አጋጣሚውን በመጠቀም በጥቃት ፈጻሚዎች የሚፈጸም ያልተፈለገ የወሲብ ድርጊት ነው። አብዛኛውን ጊዜ የወሲባዊ ጥቃት የሕግ ከለላ/ሽፋን አለው።

የጉልበተኝነት/ኃይል አዘል ጥቃት
ጭካኔ፣ አዋራጅ፣ ወይምአስፈሪ ባህሪ ወይምሥልጣንን ያለአግባብ መጠቀምዓላማ ያደረገ ግለሰቡ/ቧ ሃፍረት እንዲሰማው/ት ወይምእንዲሸማቀቅ/እንድትሸማቀቅ ማደረግ።

መድልዎ
የአንድን ሰው ማንነት ወይም ፆታን፣ ዘርን፣ ብሔርን፣ አካል ጉዳተኝነትን፣ ኃይማኖትን፣ ወሲባዊ ማንነትን የመሳሰሉ መለያዎችን ምክንያት በማድረግ ሚዛናዊ/አግባብ ባልሆነ መንገድ መረዳት/ማስተናገድ።

ይጫኑ ከጥቃት ጥበቃ ማለት ምን ማለት ነው? ለተጨማሪ ሰፋ ያሉ የጥቃት ጥበቃ ትርጓሜዎች።

ማጠቃለያ

ከጥቃት ጥበቃ ማለት ተቋማት ግለሰቦችን ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃትና ወሲባዊ ትንኮሳ እንዲሁም ከሌሎች የጉዳት ዓይነቶች ለመጠበቅ የሚወስዷቸውን እርምጃዎችን ያመለክታል። በሥራ ባልደረባ (ወይም ባልንጀራ) ወይም በተቋሙ የአሠራር ሂደቶች ወይም ፕሮግራሞች ሊደርስ ለሚችል ጉዳት መፍትሄ ይሰጣል።

በጭብጦቹ ዙሪያ ከኤፍ.ኤች.ኤፍ ጋር በሚሠሩበት ወቅት ተጠቃሚዎች እንዲሁም ማኅበረሰቡና ሠራተኞች ትኩረት እንዲሰጡት ማስቻል እንደሚኖርብዎት ከእርስዎ እንጠብቃለን።

የሥራ ቦታ ባህሪያት

ኤፍ.ኤች.ኤፍ ከተቋቋመ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ ሲሆን ከአቻ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ በመሥራት ጥሩ ስም አለው።

ከተለያዩ ምንጮች የገንዘብ ድጋፍ ያገኘ ሲሆን በሀገሪቱ መንግሥትም ከፍተኛ ምስጋና አግኝቷል። የተረጋጋ የአሠራር እና የፋይናንስ ሥርዓት እንዲኖር ያስቻለ የሥራ አመራር ቦርድ እና ከፍተኛ ልምድ ያለው የአመራር ቡድን አለው።

ነገር ግን እንዳለመታደል ሆኖ በኤፍ.ኤች.ኤፍ አስተዳደር ውስጥ የተጠቃሚዎች ተሳትፎ በቂ ትኩረት አልተሰጠውም። ይህም ጉዳይ በፕሮግራም ቀረጻ፣ በክትትልና ግምገማ ሂደቶች ውስጥ አልተካተተም።

ኤፍ.ኤች.ኤፍ የሚተዳደርበት መንገድ ለስኬታማነቱ በጣም ወሳኝ ነው። ይህም ከጥቃት ጥበቃን ማካተት አለበት። ጥሩ የሆነ ከጥቃት ጥበቃ አስተዳደር ማለት ኤፍ.ኤች.ኤፍ ለሚያገለግላቸው ተጠቃሚዎች እና ለማኅበረሰቡ ምንጊዜም ቢሆን ተጠያቂ መሆን አለበት ማለት ነው።

ሃሳብዎን ያንጸባርቁ፡- ይህ ለኤፍ.ኤች.ኤፍ ከጥቃት ጥበቃ ለምን ጉዳይ ሊሆን ቻለ?

ጠቃሚ ምክር፦

የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ ክለሳ/ግምገማ፣ የፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት እና የሪፖርት ማቅረቢያ መንገዶች ዝግጅት በመሣሉ ቁልፍ የሥራ መስኮች ላይ ተጠቃሚዎችን ማማከርና ማሳተፍ ጥሩ የሆነ ተቋማዊ አሠራር ነው። ሕጻናትን በማሳተፍ ሂደት ውስጥ ሊወሰዱ የሚገባቸው ልዩ የጥቃት ጥበቃ መሥፈርቶች አሉ።

በሁሉም ከጥቃት ጥበቃ ደረጃዎች ውስጥ ክትትል፣ ምዘና እና ትምህርት ወሳኝ ድርሻ አላቸው። የጥቃት ጥበቃ እርምጃዎች ዕቅድን መሠረት አድርገው የት ቦታ እየተተገበሩ እንደሆነ ከመገምገም ባሻገር በተሠሩ ሥራዎች ላይ ተቋማት ትምህርት እንዲያገኙ የመደገፍና ደህንነቱ የተጠበቀ መረጃ መሰብሰቡን የማረጋገጥ የተለየ ኃላፊነት አለበት።

በኤፍ.ኤች.ኤፍ ውስጥ ከጥቃት ጥበቃን በተመለከተ ኃላፊነትን የሚወስደው ማን ነው?

የኤፍ.ኤች.ኤፍ ሠራተኞች በበርካታ ቡድኖች ውስጥ ይሠራሉ። "ተቋም አቀፋዊ" አካሄድ/አሠራር እንዲኖር ለማስቻል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጥያቄ በእነዚህ የተለያዩ ቡድኖች ውስጥ የጥቃት ጥበቃ ጉዳይ ተንፀባርቋል ወይስ አልተንፀባረቀም/ተካትቷል ወይስ አልተካተተም የሚለው ነው። ይህ ማለት ከጥቃት ጥበቃ ተቋምአቀፍ ትስስር እንዲኖረው ማድረግ ነው።



1.1 ትግበራ

የኤፍ.ኤች.ኤፍ ቡድኖች ዝርዝር እነሆ። ተቋም አቀፋዊ አሠራርን ለመከተል ሁሉም ቡድኖች የጥቃት ጥበቃ ኃላፊነቶች አሉባቸው። ነገር ግን የትኞቹ ቡድኖች ወሳኝ ኃላፊነት ያለባቸው ይመስልዎታል?

ከጥቃት ጥበቃ ለማድረግ ወሳኝ ሃላፊነት አለባቸው ብለው የሚያስቧቸውን ሁሉንም የ ኤፍ ኤች ኤፍ/FHF ቡድኖች በምልክት ማድረጊያ ሳጥኖች ላይ በመጫን ይምረጡ።

ገንዘብ ማሰባሰብ	☐	ፋይናንስ	☐
ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ቦርድ	☐	የሰው ኃይል አስተዳደር	☐
ክትትል፣ ምዘና እና ትምህርት	☐	ፕሮግራሞች	☐
አስተዳደር	☐	ግንኙነት	☐

መልሶቹን ለመመልከት፣ **እዚህ ይጫኑ።**

ከጥቃት ጥበቃ

የእያንዳንዱ ኃላፊነት ነው። ነገር ግን አንዳንድ ቡድኖች ስኬታማ ለመሆን በጣም ወሳኝ ናቸው።



የቀድሞው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በጡረታ ከተገለሉበት ጊዜ አንስቶ ኤፍ.ኤች.ኤፍ፣ ዝናሽ ሀፍቶም የተባለች፣ ተቋሙን ከአንድ ወር በፊት የተቀላቀለች አዲስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ቀጥሯል።

"እዚህ እኔ በአዲስ የሥራ ድርሻ መጥቻለሁ ስለሆነም እነዚህ ሁሉ ኃላፊነቶች አሉብኝ። ሁሉም ነገር በእኔ ላይ እንደተጫነ ይሰማኛል። ስለዚህ ነገሮችን ማስተካከል ይጠበቅብኛል። በእነዚህ ጊዜያት በተለይ ከጥቃት ጥበቃ ጋር በተያያዘ ብዙ ነገሮች በትክክል ላይሄዱ ይችላሉ።"

ያስታውሱ:-

እንደ ዝናሽ ሀፍቶም የመሣሉ የድርጅት ኃላፊዎች በጥቃት ጥበቃ ፖሊሲው ውስጥ እንደተደነገገው ለተቋማዊ የጥቃት ጥበቃ የመጨረሻውን የተጠያቂነት ደረጃ ይወስዳሉ። በተጨማሪ የድርጅት ኃላፊዎች ለጥቃት ጥበቃ ጠንካራና ተጨባጭ የሆነ አመራር ሰጭነት እንዲኖር የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው። ይህም በበኩሉ ጥሩ አሠራሮችን ሊያበረታታ የሚችል ጠንካራ የጥቃት ጥበቃ ባህል እንዲፈጠር ይረዳል።

ለጥቃት ጥበቃ ጥሩ የሆነ ድርጅታዊ አስተዳደር እንዲኖር የድርጅት ኃላፊዎችና የቦርድ አባላት በጋራ መሥራት አለባቸው።

ለተጨማሪ መረጃ፣ ከጥቃት ጥበቃ እና አስተዳደር ሠነዶችን ይመልከቱ።

የጥቃት ጥበቃ የአንድ ድርጅት መሳሳ ኃላፊነት መሆኑን ዝናሽ ተረድታለች። ዝናሽ ኤፍ.ኤች.ኤፍን ከተቀላቀለች በኋላ በመጀመሪያ ደረጃ ከሠራቻቸው ሥራዎች ውስጥ አንዱ የሰው ኃይልና የአስተዳደር ኦፊሰር የሆነችውን ዚነት ሙሀባ የድርጅቱ የጥቃት ጥበቃ ዋና ተጠሪ አድርጋ መመደብ ነበር። የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲውን የማስፈጸም/ተግባራዊ የማድረግ እንዲሁም በጥቃት ጥበቃ ጉዳዮች ዙሪያ ለሠራተኞቹ ምክርና መረጃ የመስጠት ኃላፊነቱን ዚነት እንደምትወስድ ዝናሽ ገልጻላታለች።

"በጥቃት ጥበቃ ጉዳዮች ላይ ምክር የመስጠት ሃኃላፊነት ያለብኝ ሰው መሆኔ የሚገርም ነው። ጥሩ የጥቃት ጥበቃ ዋና ተጠሪ ልሆን እንደምችል ተስፋ አደርጋለሁ። ነገር ግን ምን መሠራት እንዳለበት 100% እርግጠኛ አይደለሁም። ቢሆንም ግን የሚያስደስት ሥራ ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ። በርግጥ ይህን ሥራ እንድሠራ የቀርብ አለቃዬ ጊዜ እንደምትሰጠኝና ድጋፍ እንደምታደርግልኝ አምናለሁ።"

ዚነት ይህን የጥቃት ጥበቃ አዲስ የሥራ ኃላፊነት ስትወስድ ሥልጠናና ድጋፍ ትፈልጋለች።

ወደ አገናኝ የጥቃት ጥበቃ ዋና ተጠሪ የሥራ ስምምነት ውል።

የኤፍ.ኤች.ኤፍ ቡድን አዲስ ዋና ስራ አስፈጻሚ ስላገኘ ደስተኛ ነው። ቡድኑ አሁን በአመዛኙ ጠንካራ ሆኗል፤ ምንም እንኳን ባለፈው ዓመት የማያስደስት ጊዜ የነበረ ቢሆንም። ይህም ከሥራ ቦታ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ በርካታ ቅሬታዎች እንዲነሱ አድርጓል።

የክትትል፣ ምዘና እና ትምህርት ቡድን አባል የሆኑት አሰፋ እና ደስታ ከኃይል አዘል ጥቃት ጋር በተያያዘ ያለፈውን ዓመት የቡድኑን ቸግሮች ያስታውሳሉ። በመሆኑም ከሌሎቹ የቡድኑ አባላት እኩል የሆነ የወደፊት ጥሩ ዕይታ የላቸዉም።

"ዝናሽ መልካም ስም እንዳለት አውቃለሁ፣ ነገር ግን ከባለፈው ዓመት የሰው ሃብት ግምገማ ተሞክሯችን ጋር በተያያዘ ትልቅ ሥራ ይኖርባታል/ይጠብቃታል!"

"በእርግጥ ታደርገዋለች!"



ለተጨማሪ መረጃ፣ ይመልከቱ የኃይል አዘል ጥቃትና ትንኮሳ ጠቃሚ መረጃ ሠነድ.

የሥራ ቦታ ባህሪያትን ማስተዋወቅ

ትግበራ 1.2 የሠራተኞች ባህርያትና የሥራ ቦታ ጉዳዮች

በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛው ቃል ለመሙላት በቁልቁል አመልካቹ ስር ያሉትን ዝርዝሮች ይጠቀሙ::

1. ሌሎችን በሚያሳፍር፣ በሚያዋርድ፣ በሚያቃልል ሁኔታ ወይም ቀስቃሽ/አመላካች በፍፁም አይንቀሳቀሱ::

2. አላስፈላጊ የሆኑ ቀስቃሽ/አመላካች ቅድመ ሁኔታዎች በፍፁም አያቅርቡ::

3. የስጋት ጥቆማዎች ወይም ቀስቃሽ/አመላካች መፍትሄ እንዳያገኙ በፍጹም አይፍቀዱ::

4. ወሲባዊ ተንኳሽ በሆነ መንገድ በፍፁም አይንቀሳቀሱ ወይም ቀስቃሽ/አመላካች የሆነ ወይም ክብር የሚነካ ቋንቋ አይጠቀሙ::

5. ወሲብ ቀስቃሽ/አመላካች የሆኑ ምልክቶችን በፍፁም አይጠቀሙ ወይም የሠራተኛውን/ዋን ገፅታ፣ ዕድሜ ወዘተ በተመለከተ አስተያየቶችን አይስጡ::

6. ያሉበትን የሥራ ኃላፊነት በመጠቀም በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ የሥራ ባልደረባዎትን እምነት ቀስቃሽ/አመላካች ::

መልሶቹን ለመመልከት፣ **እዚህ ይጫኑ**::

ኤፍ.ኤች.ኤፍ በምን ዓውድ/ሁኔታ ውስጥ እየሰራ እንደሆነ ያስታውሳሉ?

የማያስታውሱ ከሆነ ወይም የማነቃቂያ ሥልጠና ከፈለጉ፣ በሞጁሉ መጀመሪያ ላይ የተቀመጠውን የኤፍ.ኤች.ኤፍ መግቢያ ለመመልከት ከታች ያለውን የ + ምልክት ይጫኑ።

አጠቃላይ ሁኔታ/የመነሻ ዓውድ

ፋሚሊ ሄልዝ ፍሮንቲየርስ (ኤፍ.ኤች.ኤፍ) የጤና እንክብካቤ አገልግሎት በመስጠት ዕውቅና ያለው መካከለኛ ደረጃ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋም ነው።

ኤፍ.ኤች.ኤፍ የሚገኘዉ/የሚንቀሳቀሰው ጉልህ የሆነ የደህንነት ስጋት ባለበት ሀገር ነው። ሀገሪቱ ድህነት የተንሰራፋባት እና በአብዛኛዉ የገጠሩ ክፍል ደካማ የትምህርት ተደራሽነትና የመጀመርያ የጤና አጠባበቅ አገልግሎት የሚገኝባት ናት። የሕግ ማዕቀፎች ግለሰቦችን ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ ለመከላከል የማያስችሉና ደካማ ናቸው። በሥራ ላይ ያሉት ሕጎችም በደንብ የማይተገበሩና በቀላሉ ሊጣሱ የሚችሉ ናቸው።

ቡድኑ

ኤፍ.ኤች.ኤፍ 25 የሀገር ውስጥ ሠራተኞች አሉት። የተቋሙ የመዋቅር ቻርት የተመረጡ የቡድን አባላትን፣ በተለይ በጥቃት ጥበቃ ላይ ኃላፊነት ያለባቸውን ያሳያል።

ውጪያዊ ስጋቶችን ማስተዋወቅ

ለኤፍ.ኤች.ኤፍም ሆነ ለማንኛውም ድርጅት ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳን (SEAH) እንዲሁም ሌሎች የጉዳት ዓይነቶችን እንዴት መከላከል እንዳለባቸው እና ተቋማቸው ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በምን መልኩ መሥራት እንዳለበት ሲያስቡ ውጪያዊ ከባቢያዊ ሁኔታዎችን መረዳት አስፈላጊ ነው።

ኤፍ.ኤች.ኤፍ እየሠራ ያለው የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃትና ትንኮሳ እንዲሁም ሌሎች የጉዳት ዓይነቶች ከፍተኛ ስጋት በሆኑበት ሀገር ውስጥ ነው። ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ሀገራት በተንሰራፋ ድህነት፣ በትምህርት እጦት እና ደካማ በሆነ የሕግና የጥበቃ ማዕቀፍ ይለያሉ።

ስጋቶችን መረዳትና የሀገሪቱን የኢኮኖሚ፣ የሕግ፣ የማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና የደህንነት ሁኔታዎችን መፈተሽ ኤፍ.ኤች.ኤፍም ሆነ ሁሉም ድርጅቶች አደጋዎችን፣ ስጋቶችን እና አዲስ የሚከሰቱ ነገሮችን እንዲለዩ ይረዳቸዋል። ኤፍ.ኤች.ኤፍ ሁኔታዎችን በመተንተን፣ ሰዎች ደህንነት እንዳይሰማቸው የሚያደርጉ፣ ጥቃት አድራሾች ድፍረት እንዲሰማቸው እና ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃትና ትንኮሳ እንዲሁም ሌሎች የጉዳት ዓይነቶች እንዲፈፀሙ የሚያስችሉ ጉዳዮችን መለየት ችሏል።

1.3 ውጪያዊ የስጋት ሁኔታ ትንበያ

ስለ ኤፍ ኤች ኤፍ/FHF መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ያስቡ እና FHF ግምት ውስጥ ሊያስገባቸው የሚገቡ የጥቃት ጥበቃ ሥጋቶች ሊሆኑ የሚችሉትን ከዝርዝሩ ውስጥ ለመምረጥ ሣጥኖቹን ይጠቀሙ።

- ☐ **የወሲብ ስምምነትን የማረጋገጫ ዕድሜ**
- ☐ **ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች**
- ☐ **በሕጻናትና በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ የኃይል ጥቃቶች ዙሪያ ያለ አመለካከት**
- ☐ **የሰብዐዊ እርዳታ ሁኔታ**
- ☐ **ፆታን መረት ያደረገ መድልዎ**
- ☐ **ከፍተኛ ድህነት**
- ☐ **ልዩ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሕጻናት**
- ☐ **ደካማ የማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓት**
- ☐ **ደካማ የሆነ አካባቢያዊ አስተዳደርና ሕግ የማስፈፀም አቅም**
- ☐ **የሰዎች ሕገወጥ ዝውውር እና/ወይም የወሲብ ቱሪዝም መነሻ ወይም መዳረሻ ሀገር**
- ☐ **ደካማ የሆነ ሃገራዊ የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፍ**

መልሶቹን ለመመልከት፣ **እዚህ ይጫኑ።**

ውጫዊ ሁኔታዎች የጥቃት ጥበቃ ስጋቶችን ሊጨምሩ እንደሚችሉ አስቀድመን ተመልክተናል። በዓለም ዙሪያ፣ የዕርዳታ ሠራተኞች የጥቃት ጥበቃ ስጋቶችን ሊጨምሩ ለሚችሉ ቀውሶች ምላሽ ይሰጣሉ።

ኤፍ.ኤች.ኤፍ እየሠራ የሚገኝበት ሃገር በቅርቡ የዓለም መገናኛ ብዙኃንን ትኩረት የሳበ የጥቃት ጥበቃ ቅሌት የተከሰተበት አካባቢ በመሆኑ ውጪያዊ ስጋቶችን መረዳት በተለየ ሁኔታ ጠቃሚ ያደርገዋል።

ጋዜጣ

29th Sep 2020

70p

በኮንጎ በነበረው ሁለት አመት በፈጀው የኢቦላ መረርሽኝ ወቅት በወሲባዊ ብዝበዛ ቅሬታ የቀረበባቸው አለም አቀፍ የእርዳታ ሰራተኞች

ዲ.ኤፍ.አይ.ዲ 2018 አጭር ቪዲዮ (3 ደቂቃዎች)



ውጪያዊ የስጋት ሁኔታ ግምገማ ማካሄድ ደህንነቱ ለተጠበቀ ፕሮግራም የሚኖረውን አስፈላጊነት ለማጠናከር፣ የጥቃት ጥበቃ ቅሌት በዋናነት የተስተዋለባቸውንና ተጠቃሚዎችም ጉልህ የሆነ ጥቃት የደረሰባቸውን ተቋማት ሁኔታዎች አጉልተን ማሳየት እንፈልጋለን። በቪዲዮው ውስጥ ከጥቃት በሕይወት የተረፉ ሰዎችን ድምፅ ትሰማላችሁ።

1.4 የጥቃት ጥበቃ እውነታዎች

በጥሩ ሁኔታ ተከናውኗል- ይህን ሞጁል በማገባደድ ላይ ነዎት።

የወሲባዊ ብዛበዛ፣ ጥቃት እና የወሲባዊ ትንኮሳ በዓለም ዓቀፍ የዕርዳታ ዘርፍ ውስጥ ያላቸውን አጠቃላይ ሁኔታ እና ሥርጭት በተመለከተ ያለዎትን ግንዛቤ ለማሻሻል የተወሰኑ የመጨረሻ ተጨባጭ እውነታዎችን አሁን ያግኙ።

- በመላው ዓለም ዓቀፍ የዕርዳታ ዘርፎች ውስጥ ከወሲባዊ ብዝበዛ፣ጥቃትና ወሲባዊ ትንኮሳ ጋር በተያያዘ ሪፖርት ያለማድረግ ር የሰደደ ችግር አለ። — ሀሰት
- በዕርዳታ ሠራተኞች የሚፈፀም ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃትና ትንኮሳ በአመዛኙ በዕርዳታው ዘርፍ ውስጥ የሚስተዋል አዲስ ችግር ነው። — ሀሰት
- ባለፉት 2 ዓመታት ውስጥ 1/3ኛ የሚሆኑት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሠራተኞችና ኮንትራክተሮች ትንኮሳ አጋጥሟቸዋል። — ሀሰት
- ከአራት ሴት የዕርዳታ ሠራተኞች ውስጥ አንዷ የራ ተልዕኮዋን በመወጣት ሂደት የወሲባዊ ጥቃት እንደሚደርስባት መረጃዎች ያሳያሉ። — ሀሰት
- ዕርዳታ ከሚያገኙ ሴቶችና ልጃገረዶች ውስጥ 40% የሚሆኑት ወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እንደሚደርስባቸው ይፋ አድርገዋል። — ሀሰት

መልሶቹን ለመመልከት፣ **እዚህ ይጫኑ።**

ማጠቃለያ

ምን ተማራችሁ?

- **ከጥቃት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ቃላቶችን መተርጎም** - አሁን የጥቃት ጥበቃ እና ተዛማጅ ቃላቶችን መግለጽ ትችላላችሁ፡- SEAH፣ ወሲባዊ ብዝበዛ፣ ወሲባዊ ጥቃት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ ኃይል አዘል ጥቃት፣ ትንኮሳና አድልዎ
- በአንድ ተቋም ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ስለጥቃት ጥበቃ ኃላፊነት እንዳለበት።
- ደህንነቱ የተጠበቀ የሥራ ባህል ለመፍጠር የሥራ ቦታ ባህርያት ስለሚኖራቸው ጥቅም/ፋይዳ።

እንኳን ደስ አለዎት፣ ሞጁል 1ን አጠናቅቀዋል።

በሞጁል 2 በጉጉት እንጠብቀዎታለን። በዚያም በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትውውቅ ያደርጋሉ፡-

- የጥቃት ጥበቃ መመዘኛዎች፤
- የጥቃት ጥበቃ አቅም ግምገማ ሂደት፤ እና
- የጥቃት ጥበቃ ፖሊሲ ማዕቀፍ።

በተጨማሪም ከኤፍ.ኤች.ኤፍ ቡድን ጋር የጥቃት ጥበቃ እቅስቃሴዎችን/ዘመቻዎችን ይቀጥላሉ።

የመረጃ እና ድጋፍ ማዕከሉን ጋዜጣ፣ የጥቃት ጥበቃ መረጃዎች፣ ዌብናርስ፣ ፖድካስትስ እና ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን **ከመረጃ እና ድጋፍ ማዕከሉ** ማግኘት ይችላሉ።

በመቀጠል፤ የሞጁል 1ን ምዘና ሞልተው የRSHን ሰርተፍኬት ያግኙ

UKaid
from the British people

የኢትዮጵያ ማዕከል

መልስ

1.1 ተግባር

✓ገንዘብ ማሰባሰብ

✓ ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ቦርድ

✓ ክትትል፣ ምዘና እና ትምህርት

✓ የሰው ኃይል አስተዳደር

✓ ፕሮግራሞች

✓ ግንኙነት

እዚህ ይጫኑ። 1.1 ተግባር

1.2 ተግባር

1. ሌሎችን በሚያሳፍር፣ በሚያዋርድ፣ በሚያቃልል ሁኔታ ወይም በሚያቃ በፍፁም አይንቀሳቀሱ።
2. አላስፈላጊ የሆኑ መሲባዊ ቅድመ ሁኔታዎች በፍፁም አያቅርቡ።
3. የስጋት ጥቆማዎች ወይም ሙገጃ መፍትሄ እንዳያገኙ በፍጹም አይፍቀዱ።
4. መሲባዊ ተንኳሽ በሆነ መንገድ በፍፁም አይንቀሳቀሱ ወይም ፀያፍ የሆነ ወይም ክብር የሚነካ ቋንቋ አይጠቀሙ።
5. መሲብ ቀስቃሽ/አመላካች የሆኑ ምልክቶችን በፍፁም አይጠቀሙ ወይም የሠራተኛውን/ዋን ገፅታ፣ ዕድሜ መዘተ በተመለከተ አስተያየቶችን አይስጡ።
6. ያሉበትን የሥራ ኃላፊነት በመጠቀም በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ የሥራ ባልደረባዎትን እምነት ያለአግባብ አይጠቀሙ።

እዚህ ይጫኑ። 1.2 ተግባር

1.3 ተግባር

የውጪያዊ ስጋት ትንበያ የመልስ ወረቀት

የወሲብ ስምምነትን የማረጋገጫ ዕድሜ

ዝቅተኛ የወሲብ ስምምነት ማረጋገጫ ዕድሜ ያላቸው ሀገራት ከሕፃናት ጋር የሚደረግን ወሲባዊ ግንኙነት ሕጋዊ ያደርጋሉ። ይህም ለወሲባዊ ጥቃት ወይም ብዝበዛ ስጋት ተጋላጭ ያደርጋቸዋል። ለጥቃት የመጋለጥን ዕድል የሚያመለክቱ ባህርያት እንደ “መደበኛ” እንቅስቃሴዎች ስለሚቆጠሩ በሠራተኞች በኩል አስፈላጊው ትኩረት ላይደረግባቸው ይችላል።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች

በአንዳንድ ቦታዎች፣ በተወሰኑ ሕጻናት ወይም አዋቂዎች ላይ የሚፈፀሙ እንደ የሕጻናት ጋብቻ፣ ፆታን መሠረት ያደረግ የሃይል ጥቃት ወይም አካላዊ ቅጣት የመሣሠሉት የጥቃትና ብዝበዛ ዓይነቶች የአካባቢው ልማድ ተደርገው ሊቆጠሩ ይችላሉ። ሠራተኞችም እነዚህ ልማዶች ተቀባይነት ያላቸው እንደሆኑ አድርገው ሊያምኑ እና ሊፈፅሟቸው ይችላሉ። በተወሰኑ ሕጻናት (ለምሳሌ፣ አካል ጉዳተኛ ሕጻናት) ላይ ምክንያታዊ ያልሆነ ፍረጃ ሊያደርጉ ይችላሉ ወይም ሕጻናት በወሲብ ሥራ ለመሳተፍ ፈቃዳቸውን መስጠት እንደሚችሉ የተሳሳተ እምነት/አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል።

በሕጻናትና በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ የኃይል ጥቃቶች ዙሪያ ያለ አመለካከት

የቤት ውስጥ ጥቃት እንዲሁም በሕጻናትና በሴቶች ላይ የሚፈጸም የወሲባዊ ጥቃት በዝምታ የሚታለፍ ከሆነ፣ ሠራተኞች በሴቶችና በሕፃናት ላይ ስለሚፈጸም ጥቃት ላያውቁ ይችላሉ፣ ወይም የጥቃት ምልክቶችን ላይገነዘቡ ይችላሉ።

የሰብዓዊነት ሁኔታ

በአደጋ ጊዜ የቤተሰቦችና የማኅረሰቡ መሠረታዊ ፍላጎቶች ምላሽ ላያገኙ ይችላሉ። ለወሲባዊ ብዝበዛ ተጋላጭ ሊሆኑ ይችላሉ። በተጨማሪም ወሲባዊ ድርጊትን የምግብ፣ የመጠለያ ወይም የደህንነት ማግኛያ መንገድ አድርገው ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ቤተሰቦችና ማህበረሰቡ እርስ በእርሳቸው ላይደጋገፉ/ላይረዳዱ ይችላሉ፣ በተጨማሪም የድጋፍ አገልግሎቶችም ላይኖሩ ይችላሉ ወይም በአግባቡ አገልግሎት ላይሰጡ ይችላሉ። ፈጣን ምላሽ በሚያስፈልገው አጣዳፊ አደጋ ጊዜ ተቋማት አቋራጭ መንገዶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ ለምሳሌ- የሠራተኞችን የኋላ ታሪክ ሳያረጋግጡ መቅጠር፣ ወይም በቂ የሆነ የስጋት ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት ባለማድረግ። እነዚህን አቋራጭ መንገዶች መጠቀም የፕሮግራሙን ደህንነት ጥያቄ ውስጥ ሊያስገባው ይችላል።

ፆታን መሠረት ያደረገ መድልዎ

ሴቶችና ልጃገረዶች ዝቅተኛ/አነስተኛ አቅም ካላቸው ለወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ በይበልጥ ተጋላጭ ይሆናሉ። አመኔታ ላያገኙ ስለሚችሉ ወይም ለተጨማሪ መገለል ሊዳረጉ ስለሚችሉ ገልጸው መናገር እንደማይችሉ ሊሰማቸዉ ይችላል።

ከፍተኛ የድህነት ደረጃዎች

በድህነት መኖር ሰዎችን ለወሲባዊ ብዝበዛ ሊያጋልጣቸው ይችላል። እንዲሁም መሠረታዊ ፍላጎቶችን ከማኅበረሰቡ እና ከሠራተኞች ለማግኘት ሲሉ ወሲብን እንደመጠቀሚያ መንገድ አድርገው ሊወስዱ ይችላሉ። ሕጻናት የመሥራት ግዴታ ሊኖርባቸው ይችላል፤ እንዲሁም ተቋሞች ወይም አቅራቢዎቻቸው የሕጻናትን ጉልበት ሊጠቀሙ ይችላሉ።

ልዩ ጥበቃ የሚያስፈልጋቸው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሕጻናት

አካል ጉዳት ያለባቸው ሕጻናት (እና አዋቂዎች)፣ ከኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ጋር የሚኖሩ፣ ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ፣ ስደተኞች ወይም በጎዳና ላይ የሚኖሩ ወዘተ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚደርስባቸውን መሸማቀቅ፣ መገለል፣ መድልዎ እና የድጋፍ እጦት የመሣሠሉ ከፊል ምክንያቶች ተከትሎ ለጥቃት የመጋለጣቸው ዕድል እየጨመረ ነው። ሠራተኞችም እነዚህን ምክንያት አልባ ፍረጃዎች/የተሳሳቱ አመለካከቶች ሊጋሩ ይችላሉ፤ በመሆኑም ጥቃት ሲመለከቱ ምንም ሳያደርጉ ይቀራሉ።

ደካማ የማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓት

ደካማ የማኅበራዊ ዋስትና ሥርዓት ባለበት ሁኔታ በአካባቢያዊ ባለስልጣናት ለሚፈጸሙ ጥቃቶች ሁሉ ምላሽ ለመስጠት እምነት የሚጣልባቸው አይሆኑም።

ደካማ የሆነ አካባቢያዊ አስተዳደርና ሕግ የማስፈፀም አቅም

ደካማ የሆነ አካባቢያዊ አስተዳደርና ሕግ የማስፈፀም አቅም ባለበት ሁኔታ በፖሊስና በፍርድ ቤቶች የሚፈፀሙ ጥቃቶች ሪፖርት የመደረጋቸውና ምላሽ የማግኘታቸው ዕድል አነስተኛ ነው።

የሰዎች ሕገ ወጥ ዝውውር እና/ወይም የወሲብ ቱሪዝም መነሻ ወይም መዳረሻ ሃገር

ሠራተኞች ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ ሕጻናትና አዋቂዎች ያላቸውን ተደራሽነት በመጠቀም በስጋት ውስጥ ያሉ ሕጻናትና አዋቂዎች ያሉበትን ቦታ በማመላከት በሕገ ወጥ ዝውውር ሊሳተፉ ይችላሉ።

ደካማ የሆነ ሃገራዊ የሕግና የፖሊሲ ማዕቀፍ

ጥቃቶች ሪፖርት የመደረጋቸውና ምላሽ የማግኘታቸው ዕድል አነስተኛ ነው።

የአካባቢ ስጋት ግምገማ ማድረግ ሁሉም ዓይነት ስጋቶች ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኙ ለማረጋገጥ ሊረዳ ይችላል። ይህም የጥቃት ጥበቃ መሥፈርቶች ባለማስተዋል ሊታለፉ የሚችሉ ክፍተቶችን በመሙላት ሌሎችን ሆን ብለው ለማጥቃት በፈለጉ አካላት መጠቀሚያ እንዳይሆኑ ለማረጋገጥ ይረዳል።

እዚህ ይጫኑ። 1.3 ተግባር

1.4 ተግባር

በእርዳታ ሠራተኞች የሚፈጸም የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እናየወሲባዊ ትንኮሳ (SEAH)	**ሀሰት**	አይ.ዲ.ሲ ሪፖርት (2018) ወሲባዊ ብዝበዛ እና ጥቃት በዕርዳታ ዘርፍ ውስጥ።
በመላው የዓለም ዓቀፍ የዕርዳታ ዘርፍ ውስጥ የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና የወሲባ ትንኮሳን ሪፖርት ያለማድረግ ሥር የሰደደ ችግር አለ።	**እውነት**	ግኝት ከ ግኝት ከ የዲ.ኤፍ.አይ.ዲ የማዳመጥ ልምምድ (2018) የወሲባዊ ብዝበዛ፣ ጥቃት እና የወሲባ ትንኮሳ በ ዓለም ዓቀፍ የዕርዳታ ዘርፍ፡- የጥቃቱ ተጎጂዎች እና ከጥቃት በሕይወት የተረፉ ሰዎች ድምፅ።
ከአራት የዕርዳታ ሴት ሠራተኞች ውስጥ አንዷ የሥራ ተልዕኮዋን በመወጣት ሂደት ውስጥ የወሲባዊ ጥቃት እንደሚደርስባት የወሲባዊ ጥቃት እንደሚደርስባት መረጃዎች ያሳያሉ።	**እውነት**	በሰብዓዊ እንዲሁም በልማት ዕርዳታ ሠራተኞች ላይ የሚደረግ ወሲባዊ ጥቃት ይቁም 2017 ሪፖርትን (ቱፍትስ ዩኒቨርስቲ) መሠረት አድርጎ በቀረበ መረጃ –
በሶሪያ ተከስቶ በነበረው ቀውስ፣ 40% የሚሆኑትእርዳታ የሚያገኙ ሴቶችና ልጃገረዶችበሰብዓዊ ዕርዳታ ወቅት ወሲባዊ ብዝበዛና ጥቃት እንደሚደርስባቸው ይፋ አድርገዋል።	**እውነት**	ከአይ.አር.ሲ ሪፖርት ውስጥ በተገኘ መረጃ መሠረት፡- በመላው ሶሪያ ፅታን መሠረት ያደረገ ጥቃት የሚፈጸምበት አካባቢ ኃላፊነት (2017)
አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሠራተኞች እናየወሲባዊ ትንኮሳ እንደሚደርስባቸው ኮንትራክተሮች ሪፖርት አድርገዋል በ2017 እና 2019 መካከል።	**እውነት**	የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የወሲባዊ ትንኮሳ ጥናት በ በሥራ ቦታችን፣ በ 2019 የታተመ ሪፖርት

እዚህ ይጫኑ። 1.4 ተግባር


የድርጅቱ መሪ/ሃላፊ
ዝናሽ ሀፍቶም
ሰው ሃይል አስተዳደር
ዚነት ሙሀባ
ግምገማ፤ ምዘናና ትምህርት ሃላፊ
አሰፋ ጌታቸው
ፕሮግራም ማናጀር
አህመድ መሐመድ
ግምገማ፤ ምዘናና ትምህርት ኦፊሰር
ደስታ ውሂብ
ፕሮግራም ኦፊሰር
አስቴር ዘማች

እዚህ ይጫኑ።